# ቅንጅት ሰሜን አሜሪካ የድጋፍ ድርጅቶች ማሕበር

**KINIJIT** NORTH AMERICA ASSOCIATION OF SUPPORT **ORGANIZATIONS (KNAASO)**

766 Rock Creek Church Rd. NW Washington DC. 20010

Tel: (202) 541 0556 Fax: (202) 541-0557 Email: kinijitna@kinijitna.org


ፌብሩዋሪ 24 ቀን 2008 ዓ/ም

## <u>የቅንጅት ሰሜን አሜሪካ የድጋፍ ድርጅቶች ማሕበር 5ኛ ጠቅላላ ጉባኤ የጋራ መግለጫ</u>

ከአስራ ስምንት የቅንጅት ሰሜን አሜሪካ የድጋፍ ድርጅቶች ማሕበር የተወከልን ያመራር አባላት በላስ ቬጋስ ከተማ ፌብሩዋሪ 23 እና 24 2008 ዓ/ም በዓይነቱም ሆነ በጥራቱ የላቀ ስሜት የታየበት ስብሰባ ካካሄድን በኋላ ቀጥሎ ከተዘረዘሩት ግንዛቤዎችና ስምምነቶች ላይ ደርሰናል።

1. ሰብአዊና ዲሞክራሲያዊ መብቶች የሚከበሩባት፤ በእኩልነት ላይ የተመሠረተ አንድነት የሰፈነባት እናት ሀገር ለመገንባት የኢትዮጵያ ሕዝብ እያካሄደው ያለውን ትግል ከምን ጊዜም በበለጠ ተጠናክረን እንደግፋለን።
2. በ1997 ዓ/ም የተከናወነው ምርጫ መልካም ፍሬ ሊያሳይ ከተዳረሰ በኋላ በመንግሥት አፈናና ግድያ ፈሩን ስቶ ባሁኑ ሰዓት ሀገራችን የቁም እሥር ቤት ሆና ትገኛለች። የሚካሄደው አፈና ተመክሮ የጎደለው የታሪክን ጉዞ ለማቆም የሚደረግ ሙከራ ስለሆነ ውጤት አልባና ሀገራችንን ለበለጠ አደጋ የሚያጋልጥ መሆኑን እናስገነዝባለን።
3. ቅንጅት ለአንድነትና ለዴሞክራሲ ፓርቲ የኢትዮጵያ ሕዝብን ተደራራቢ የፖለቲክ፤ የማሕበራዊና የኤኮኖሚ ችግሮች ያገናዘበና የወደፊቱን ብሩህ ተስፋ ያመላከተ ራዕይ አለው። አሁንም ቢሆን ሠላማዊ የትግል መርህን የተከተለ ስልት ለመቀጠል መወሰኑን ከልብ እንደግፋለን።
4. መንግሥት ከሚያካሂዳቸው መሰሪ ተግባሮች አንዱ ቅንጅት ለአንድነትና ለዴሞክራሲ ፓርቲን ለማጥፋት፤ ይህ የማይቻል ከሆነ ደግሞ የፓርቲውን ስምና አርማ ለሌሎች ሰጥቶ ለማዳከም ነው። ከእስር የተፈቱት የቅንጅት መሪዎችም በፖለቲካው መድርክ እንዳይንቀሳቀሱና ከሚደግፋቸው ሕዝብ ጋር እንዳይገናኙ ስብሰባ አዳራሽ እንኳ የመከራየት መብታቸውን ነፍጓል። ከዚህ የበለጠ አምባገነንነትና ፀረ ዴሞክራሲነት ሊኖር እንደማይችል የኢትዮጵያ ሕዝብ በግልጽ ስለሚያውቅ በሕዝብና በቅንጅት መሀከል ያለውን ቁርኝት ለመስበር መንግስት የሚያደርገው ሙከራ ውጤት አልባ እንደሚሆን እናረጋግጣለን።
5. መንግሥት የቅንጅትን ስምና መለያ ነጥቆ ለሌሎች በመስጠት የትግሉን ርምጃ የሚገታ ቢመስለውም የኢትዮጵያ ሕዝብ ቅንጅትን የሚደግፈው ስለአርማው ሳይሆን ስለዓላማው ነውና የቅንጅት አመርራ የዲሞክራሲ ትግሉን እንደገና ለማቀጣጠልና ወደፊት ለመሄድ የስም ለውጥ ማድረግ አስፈላጊ ከመሰለው ድጋፋችን የማይለየው መሆኑን እናረጋግጣለን።
6. በሀገራችን የሰፈነው የፖለቲካና የሰብአዊ መብት አፈና ብቻ ሳይሆን ሕዝባችን ይህ ነው ለማይባል የኤኮኖሚ ድቀት ተዳርጓል። ለዚህም ከመንግሥት የፈጠራ መግለጫዎች ባሻገር ከዳር እስከዳር በግኡዝ የሚታየውንና እየተባባሰ ያለውን ድህነት በማስረጃነት ማቅረብ ይበቃል። የኤኮኖሚው ድቀት ለሚያስከትለው ማሕበራዊ ቀውስ ተጠያቂው በሥልጣን ላይ ያለው መንግሥት እንደሚሆንም ጥርጥር የለውም።
7. ለነጻነት የሚደረገው ትግል በዚህ ዙሪያ የሚታገሉ ኃይሎችን ትብብር ስለሚጠይቅ በመሀከላቸው ያለውን አነስተኛ ልዩነት ወደጎን አድርገው በሕብረት ለመሥራት የሚያስችላቸውን ምቹ ሁኔታ ውለው ሳያድሩ እንዲፈጥሩ ጉባኤያችን ጥሪውን ለዴሞክራቲክ ኃይሎች ሁሉ ያስተላልፋል

8. የኢትዮጵያ መንግሥት በሀገሪቱ ውስጥ እየተከማቸ ላለው እምቅ ቀውስ ጆሮ ዳባ ልበስ ማለቱን ትቶ አግባብ ካላቸው ጋር ለመሥራት በሚያስችል ብሔራዊ ጉባዔ ውስጥ ተሳታፊ እንዲሆንና ሀገራችንን የዘላቂ ሠላምና ልማት ባለቤት በማድረግ ረገድ የበኩሉን አስተዋጽኦ እንዲያደርግ ጥሪያችንን እናስተላልፋለን።

ከላይ የተዘረዘሩትን ግንዛቤዎች መነሻ በማድረግ በውጭ አገር የምንኖር ኢትዮጵያውያን፤ በተለይም በማሕበሮቻችን ዙሪያ የተሰባሰቡ ወገኖቻችን ድምጽ ላጣው ወገናቸው ድምጽ የሚሆኑበት ጊዜ አሁን እንደሆነ ተገንዝበናል። በዚህ ረገድ ቅንጅትን በዲፕሎማሲውና በፋይናንስ መስክ ለማጠናከር እንዲሁም ሠላማዊ ትግሉን በአፋጣኝ እንዲቀጥል በሚያስፈልጉት ግብአቶች ሁሉ ለመርዳት ቃል ገብተናል። ይህን ለማድረግ ይቻል ዘንድም ማሕበራችን ከምንጊዜም በተሳለ ስልትና ቅንብር የሚመራበት መዋቅር ዘርግቶ ወደተግባራዊ እንቅስቃሴ እንደተሸጋገረ ማረጋገጥ እንወዳለን።

ቅንጅት ሰሜን አሜሪካ የድጋፍ ድርጅቶች ማሕበር 5ኛ ጠቅላላ ጉባዔ
ላስ ቬጋስ (ኔቫዳ)